የሰ/መ/ቁ. 37105

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር

መላኩ መለሰ /ነገረ ፡ ፈጅ/ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ሰሎሞን አበበ ኮከብ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተውም የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል፤ ስለዚህ ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ እና ያልተሰጠኝ የዓመት ፈቃድ ተሰጥቶኝ ወደስራዬ እመለስ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ በተደነገገው መሠረት የስራ ውል ሊያቋርጥ የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ነው፤ ለአምስት የስራ ቀናትም በስራው ላይ ሣይገኝ ቀርቶአል በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው ይመለስ፤ ለመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት የሚገባውን የዓመት እረፍትም በማካካሻ እረፍት መልክ ይሰጠው በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ቢከራከርም፤ አመልካች ግን የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈፀመው የስራ ውልን የሚያቋርጥ ድርጊት ምክንያት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአመልካቹ ክርክር እንደተገለፀው ተጠሪ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ በፖሊስ ምርመራ ተደርጎበታል፡፡ የተጠሪ ስራ የሎደር ኦፕሬተርነት ሲሆን፤ 120 ሊትር ናፍጣ ወስዶ ለግል ጥቅሙ አውሏል በሚል ነው በፖሊስ ተይዞ ምርመራ ሊጣራበት የቻለው፡፡ በዚህ ምክንያት ታስሮ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የቆየ ሲሆን፣ ከተለቀቀ በኋላም ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ሥራው ላይ ሣይገኝ እንደቀረ በአመልካች ክርክር ተገልጿል፡፡ የእምነት ማጉደልን በተመለከተ አመልካች የቆጠረው ማስረጃ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይህን የምርመራ መዝገብ አስቀርቦ አልተመለከተም፡፡ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በራሱ በቂ አስረጂ ሊሆን አይገባም በሚል ሣያስቀርበው እንደቀረ ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራው ላይ አልተገኘም የሚለውን ክርክር በተመለከተም ፍ/ቤቱ በቂ የሆነ ማጣራት ሣያደርግ እንዳለፈው ነው ውሣኔው የሚያሣየው፡፡

በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ወይም ያልተማመኑበት የፍሬ ነገር ነጥብ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ በአግባቡ መሰማት አንዱና ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርዓት መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ በእርግጥ በተከራካሪ ወገን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ ያለምንም ምክንያት መሰማት አለበት ማለት አይደለም፡፡ የተቆረጠው ማስረጃ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ ውድቅ የሚደረገው እንዲሁ በደፈናው ሣይሆን፣ ምክንያቱን በግልጽ በጽሑፍ በማስፈር ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ.138/፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው የስር ፍ/ቤቶች ወደ ውሣኔ ያመሩት በአመልካች የተቆጠረውን ማስረጃ አስቀርበው ሣያዩ እና ሣይመረምሩ ነው፡፡ ማስረጃው በፖሊስ ምርመራ የተደረገበት የምርመራ መዝገብ ሲሆን፣ ይህም ቢያንስ ተጠርጣሪው /ተጠሪ/ የሰጠው ቃል፣ ተፈፀመ ስለተባለው ወንጀል በተመለከተ የተሰሙ ምስክሮች፣ የመርማሪውን አስተያየት ወይም ግኝት እንደሚይዝ ይገመታል፡፡ አመልካች የምርመራ መዝገቡን በአስረጂነት የቆጠረውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ መገመት የሚያስቸግር አይደለም፡፡ በመሆኑም ፈራጅ የሆነው አካል (ፍ/ቤቱ) ይህን መዝገብ አስቀርቦ ሣይመለከትና ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ ሊደርስ አይችልም፤ አይገባምም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ያየነው ከስራ መቅረትን በተመለከተ የተነሣውን ክርክር ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህን ነጥብ ያለፈው ተጠሪ የቀረው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ስለነበር ነው በሚል ነው፡፡ እዚህ ድምዳሜ ላይ ሊደርስ የቻለበትን ምክንያት ግን በዝርዝር አልገለፀም፡፡ ተጠሪም በዚህ ድምዳሜ እንደማይስማማ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር ገልጿል፡፡ ከስራ ቀረሁ የሚለው በመታሰሩ ምክንያት ሣይሆን፣ ታሞ ሐኪም ቤት ሲመላለስ /ሲታከም/ ስለነበረ ነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት ፍ/ቤቱ ወደ ውሣኔ ያመራው ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣይሰማ እንደሆነ ነው፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ /ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ ዋነኛው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## **<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21629 ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 60830 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብ ቁ. 21629 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ እና በአመልካች የተቆጠሩትን ማስረጃዎች በመስማት ክርክሩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡ ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ